# የሁለት ደቂቃዋ የኢቲቪ ዘገባ
# ሕወሃት እራሱን መሳቂያ አደረገ

አማኑኤል ዘሰላም
work_amanuel@yahoo.com

የካቲት 20 ቀን 2001

የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አመራር አባላት በድርጅቱ ጽ/ቤት ለአገር ዉስጥና ለዉጭ አገር ጋዜጠኞች፣ በድርጅቱ ላይ እየከፋ የመመጣዉን የሰብዓዊ መብት ረገጣና ሕገ ወጥ እርምጃ በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርበዋል። የአንድነትን ጋዜጣዊ መግለጫ ተከታትሎ ለሕዝብ ለማቅረብ በጽ/ቤቱ ከመጡት ጋዜጠኞች መካከል በሕዝብ ገንዘብ የሚንቀሳቀሰዉ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ነበር።

የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ባልደረቦች ካሜራቸዉን ይዘዉ ስብሰባዉ ተጀምሮ እስኪያልቅ ይቀርጹ ስለነበረ «ስለ ጋዜጣዊ መግለጫ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ዛሬ ማታ ሳይዘግብ አይቀርም። » ብለዉ የሚናገሩ ሰዎች ነበሩ። እኔም «እስቲ መሻሻል እንዳለና እንደሌለ እናያለን» ብዬ ብዙም ቦታ ሳይሰጠዉ አለፍኩት።

የኢቲቪ ባልደረቦች የአንድነት ጽ/ቤት ድረስ ካሜራዎቻቸዉን ይዘዉ ፣ ለሰዓታት የፈጀ ስብሰባ አዳምጠዉ ፣ ወጥተዉ፣ ወርደዉ በቴለቭዥን ለማቅረብ የቻሉት 2 ደቂቃ ከሃያ አምስት ሴኮንድ የሚፈጅና ዶ/ር ያዕቆብና አቶ ደበበ እሸቱ የሃሳብ ልዉዉጥ ሲያደርጉ የሚያሳይ ዘገባ ነበር። ያ ሁሉ ወጣ ወረድ ለሁለት ደቂቃ !!!!!! አያስቅም።

የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ ባልደረባ በሥፍራዉ ተገኝቶ ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርቧል። አወደ ኢትዮጵያ ባቀረበዉም ልዩ ዘገባ የጋዜጣዊ መግለጫዉን ይዘት በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን፣ ፓርቲዉ ያወጣዉ መግለጫም ይፋ ሆኗል።

የአንድነት አመራር አባላት በተለይም በወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ላይ በማዕከል ደረጃ ገገርዉ ፓርቲ እየወሰደ ያለዉን ሕገ ወጥ እርምጃ ያወገዙ ሲሆን፣ በአንድነት አባላት ላይ የገገርዉ ፓርቲ የክልሉ ባለስልጣናት እያደረሱት ያለዉን እንግልትም በአራት ክልሎች (ምሥራቅ ጎጃም፣ ወላይታ ፣ ሳዉላና ኢሊባቡር) የመጡ የፓርቲዉ አስተባባሪዎች በመረጃ አጋልጠዋል። ምርጫ 2002 እንዲሁም መድረክን በተመለከተ ገለጻዎች ቀርበዋል። ምርጫዉ ፍትህዊና ነጻ ካልሆነ አንድነት እንደማይሳተፍ የፓርቲዉ አባላት አረጋግጠዋል።

የቀድሞ የቅንጅት መሪዎች ከእሥር ስለተፈቱበት ሁኔታም ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የአመራር አባላቱ የፈረሙት ፊርማ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዳሉት የጥፋት ዉሳኔ ከተወሰነ በኋላ እንደሆነ ገልጸዉ በእሥር ቤት በተለያዩ ቦታዎች ታስረዉ

ስለነበረ ገዢዉ ፓርቲ የተለያዩ ወረቀቶች ለተለያዩ ሰዎች እንዳስፈረመ ለማብራራት ተሞክሯል።

በዚህ ጊዜ ነበር አቶ ደበበ እሸቱ «ስለእኔ ጉዳይ እኔዉ እናገራለሁ» ሲሉ ሃሳባቸዉን የገለጹት። እንደዚህ ማለታቸዉ ምኑ ላይ ችግር እንደሆነ አይገባኝም። ሃሳብ ማቅረብና መከራከር አይችሉም እንዴ ? የፖለቲካ መድረክ እኮ ነዉ - ቅዳሴ እኮ አይደለም !

**እንግዲህ አስቡት የጋዜጣዊ መግለጫ 99.9 በመቶ የሚሆነዉን ቆርጠዉ ፣ ሁለት ደቂቃ የምትሆን፣ ከፓርቲው ጋር ግንኙነት በሌለዉ፣ ከተሳታፊ በተጠየቀ፣ ባለፈና ተራ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገውን የሃሳብ ልዉዉጥ እንደ ትልቅ ድክመት በመቁጠር ነዉ እነ አቶ በረከት ስምኦን አንድነት ፓርቲ ላይ እንደለመዱት ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ለመስራት የሞከሩት። አላወቁትም እንጂ እራሳቸዉን ነዉ መሳቂያ ያደረጉት። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዉም ጆሮዎቹ የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ ላይ ነዉ። እነርሱን የሚያዳምጥም የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋዜጣዊ መግለጫዉን ሂደት በሚገባ ተከታትሎታል። የአንድነት ፓርቲ ሕዝቡ ዉስጥ ያለ እንደመሆኑ ስለ አንድነት ፓርቲ መረጃ ከነ አቶ በረከት አይጠብቅም።**

ያ ብቻ አይደልም። ከዚያ ሁሉ ጋዜጣዊ መግለጫ በአንድነት ላይ ሊያወጡበት የቻሉት ይች አስቂኝ የሁለት ደቂቃ ንግግር ብቻ ከሆነች በርግጥ የአንድነት ፓርቲ ያቀረባቸዉን አንኳር የፖለቲካ ጥያቄዎችን የመመለስ አቅም እንደሌላቸዉ ያሳያል ማለት ነዉ።

የአንድነት ፓርቲ የአገሪቷን ሕግ በመጥቀስ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደዉን እርምጃ አግባብነት እንደሌለዉ በሰፊው አብራርቷል። ኢቲቪ ሕግ ያገናዘበ ዘገባ በማቅረብ አንድነት ፓርቲ ያቀረነበዉንና የፍትህ ሚኒስቴር የሚለዉን ለማስተያይት ሞክሯል ? አልሞከረም።

አንድነት በክልል ደረጃ ጽ/ቤቱ እየተዘጋ እንደሆነና አባላቱ እየተንገላቱ እንደሆነ በመረጃ አስርድቷል። ኢቲቪ የሚመለከታቸዉን የክልል ባለሥልጣላንት አነጋግሮ በአንድነት ፓርቲ የቀረበዉ መግለጫ እዉነተኝነትን ለማረጋገጥ ሞክሯል ? አልሞከረም።

ይህች የሁለት ደቂቃ አስቂኝ ዘገባ እነ አቶ በረከትን ትዝብት ዉስጥ ከመጣሏ ባሻገር ምን ያህል ገዢዉ ፓርቲ የአንድነት ፓርቲ እንደሚፈራ ታሳያለች። የአንድነት ፓርቲ በኢቲቪ ጥቂት ሰዓት በሳምንት ቢሰጠዉ ሕዝብን ከዳር እስከ ዳር እንደሚያነቃንቅ ያወቃሉ። የአንድነት ፓርቲ ስብሰበ ማድረግ ቢፈቀድለት በሺዎች የሚቆጠሩ ትግራይ ዉስጥ ሁሉ ሳይቀር በየክልሉ መሰብሰብ እንደሚችል ያወቃሉ። እነርሱ ከሕዝብ ተደብቀዉ በሌሊት ሲጓዙ፣ የአንድነት መሪዎች ከሕዝቡ ጋር ተቀላቀልዉ የሚዉሉ እንደሆኑ ያወቃሉ።

እነርሱ የተጣሉት ወይንም ሃሳባቸዉን የማይቀበል (ከነርሱም ጋር የነበረም ቢሆን) እንደጠላት ቆጥረዉት ያስወግዱታል። ያጠፉታል። (የአወሬነት ባህሪ ይሉታል ይሄ

ነዉ)። በእንደነ አቶ ስዬ አብርሃና ጄነራል ጻድቃን ገብረእግዚብሄር ላይ የተወሰደዉ እርምጃ የሚያሳየዉ ይሄንኑ ነዉ። ዛሬም በኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉ ባለስልጣናት በፓርቲዉ የሚደረገዉ ብዙ ስህተቶች እየተደረጉ እንዳለ ቢያወቁም የመቃወም ብርታት የላቸዉም። ለምን ኢሕአዴግ ዉስጥ በሃሳብ መለያየት መጨረሻዉ መወገድ ነዉ። ስለዚህ እንዳይወገዱ ይፈራሉ። ዝም ያላሉ።

የአንድነት መሪዎች ጋር እንደዚህ የለም። የሚያራምዱት ሊበራል ዲሞራሲ ነዉ። ሚስጥራዊ አሰራር የላቸዉም። በግልጽ ነዉ የሚንቀሳቀሱት። ሲወያዩ በነጻነትና በሰለጠነ መልኩ ነዉ፡ ልዩነትም ካላቸዉ «አልስማም፣ አልቀበልም። ትክክል አይደለህም» ይባባላሉ። ተፈጥሯዊ ነዉና አንዳንዴ የሚፈጠር የሃሳብ ግጭት ወንድማማችነታቸዉ፣ ወዳጅነታቸዉና አጋርነታቸዉን አያበላሸዉም። አንድ ተራ አባል በድፍረት በይፋ አመራሩ በይፋ የመቃወም መብት አለዉ። ታምኝ አልሆንክም ተብሎ አይወቀስም።

እጅግ በጣም ወዳጆች በሆኑ በአቶ ደበበ እሸቱና በዶር ያእቆብ መካከል ለሁለት ደቂቃ የተደረገዉ የሃሳብ ልዉዉጥ እንደ ትልቅ ነገር ተቆጠሮ በኢቲቪ እነ አቶ በረከት እንዲቀርብ ሲያደርጉ ፣ በግልጽ የምናየዉ ምን ያህል ኢሕአድጎች ያልበሰሉ ዲሞክራሲ የማይገባቸዉ፣ በራሳቸዉ የማይተማመኑ እንጭቾች መሆናቸዉ ነዉ። እኔ ለነርሱ አዘንኩላቸዉ።በርግርጥ እራሳቸዉን ነዉ ያስገመቱት። (የኢሕአዴግ ካድሬዎች በአቶ ደበበን በዶ/ር ያዕቆብ መካከል የሌለን ጠብ ለመፍጠር ከሆነ ሃሳባችዉ መንገዳቸዉን ጨርቅ ያርግላችዉ :) )

እንግዲህ በአንድነትና በኢሕአዴግ መካከል ያለዉን የአሰራር ልይነት ካሳየሁ ዘንዳ አሁን ኢቲቪ በምን መልኩ መንቀሳቀስ እንደነበረበት የሚገልጽ ክፍል፣ ከሕገ መንግስቱ በማንሳት ጥቂት ብዬ እደመድማለሁ።

አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 5 በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደር የመገናኛ ብዙሃን በአገሪቷ ያሉትን የተለያዩ አስተያየቶች በእኩልነት ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል። ሕገ መንግስቱ የአገሪቷ የበላይ ሕግ ነዉ። የፌደራልም ሆነ የክልል ባለሥልጣናት ሕገ መንግስቱን የማስከበር ግዴታ አለባቸዉ።

የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በተለይም አቶ መለስ ዜናዊ በድፍረት ነዉ ድርጅታቸዉ ለሕገ የቆመ እንደሆነ የሚናገሩት። ታዲያ አንቀጽ 29 እነ አቶ መለስና በረከት ወዴት ነዉ ያደረጓት ? ነዉ ወይስ እነርሱ እኛ የማናወቀዉ የተለየ የሕገ መንግስት ሰነድ አላቸዉ ? አቶ መለስ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ እንዳለ በኢቲቪ ተላልፎላቸዉ የአንድነት ፓርቲ ጋዜጣዊ መግለጫ ግን 99% ተቆረጦ 1% ብቻን ማቅረቡ አንቀጽ 29 መተግበር ይባላል?

ኢቲቪ በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደር መሆኑ የሚታወቅ ነዉ። ከግንቦት ሰባት በኋላ ኢቲቪ ሙሉ በሙሉ የገዢዉ ፓርቲ የፖሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ሆኗል። ጠዋትም ማታ ልክ በኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ጊዜ እንደነበረዉ የኋላ ቀር ፕሮግራም ነዉ የሚያቀርቡት። «ኢሰፓ» የሚለዉ በ«ኢሕአዴግ»፣ «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ» የሚለዉን «ፕሬዘዳንት መንግስቱ ኃይለማሪያም፣ የኢሰፓ

ዋና ጸሃፊ፣ የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ...» በሚለዉ፣ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች» የሚለዉን « የኢትዮጵያ ሕዝብ» በሚለዉ ብንቀይረዉ ያኔ በደርግ ጊዜ የነበረዉና አሁን ያለዉ የኢቲቪ ፕሮግራም አንድ ሳይህን አይቀርም።

እንግዲህ አስቡት ምን ያህል ወደ ኋላ እንደቀረን! ይህንን ነዉ እንግዲህ ዲሞክራሲ አመጣንላቹህ የሚሉን ? ይህንን ነዉ እንግዲህ "የሕዝብ ብሲት የካቲት 11 የወለደዉ" ሕወሃት ለሁላችንም ጥቅም ቆመልን የሚሉን ?